# *ኢትዮጵያ የህዝቦች መታጎሪያ እስር ቤት እንጂ በመፈቃቀድ የተገነባች የጋራ ሃገራቸው ኣይደለችም*

ኢትዮጵያ በሃይል ከተመሰረተችበት ወቅት ኣንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ የተለያዩ ህዝ
ቦች በሃይል የታጎሩባት እስር ቤት መሆኗ የሚያከራክር ኣይደለም። ዛሬ በኢትዮ
ጵያ ውስጥ የሚጠሩ ህዝቦች በራሳቸው መልካም ፈቃድ ተቀራርበው በመሰረቱት
የጋራ ሃገር ኣይደለም እየተዳደሩ ያሉት። በነፍጠኛው ወራሪ ሃይል ኣንድ ላይ
ተጨፍልቀው በግድ ኣንድ ሃገር ለመባል ተገደዱ። ዛሬ ነፃነቷን ኣውጃ ሉኣላዊት
ሃገር ለመባል የበቃችዋን ኤርትራ ጨምሮ የኢትዮጵያ ህዝቦች የፖለቲካ ታሪክ
በሃይል ኣንድ ላይ የመገዛት ታሪክ ነው።

የምኒሊክ ጦር ነፃ ህዝቦችን በሃይል ወደ ኣቢሲኒያ ኣስተዳደር ለመጠቅለል በዘመ
ተበት ወቅት ህዝቦች የኣበባ ጉንጉን ይዘው በእልልታ ኣልነበረም የተቀበሉት።
በጦር፣ በጎራዴና በመንጫ ለህዝባቸው ነፃነትና ለሃገራቸው ሉኣላዊነት ሲሉ በጀግ
ንነት ወረራውን ለመመከት ተዋደቁ። እጅግ መራራ መስዋእትነቶችን በመክፈል
ሃገራቸውንና ህዝባቸውን ከነፍጠኛው ወራሪ ሃይል ለመታደግ ተፋለሙ። በኦሮም
ያ እንደ ጨለንቆ፣ ኣኖሌና ሸገር ባሉ ኣካባቢዎች የተካሄደው የኣንገብርም ፍልሚ
ያ ለዚህ ሃቅ ኣብይ ምሳሌ ነው። የምእራብና የሰሜን ኦሮምያ የወቅቱ የኦሮሞ
ንጉሶችም ቢሆኑ በሰላማዊ መንገድ ኣንዳንድ ኣመፆችን ኣካሄደው በመጨረሻ ለእ
ስራትና ለከፍተኛ ግብር ቅጣት መዳረጋቸው የዚሁ ራስን የመከላከል እንቅስቃሴ
ኣካል ነበር። የወሎውን መሃመድ ኣሊ (ንጉስ ሚካኤል) የመሳሰሉት ደግሞ
ጦራቸውን በማሰለፍ የነፍጠኛውን ወራሪ ሃይል እስከመፋለም ደርሰው ነበር።
እንደ መስታወት፣ ወርቂቱ፣ ኣሊ ጉዋንጉል፣ ጉግሳ ወሌ፣ ዋቅሹም ጎበዜና ልጅ
ኢያሱ ባሉ የኦሮሞ ጀግኖች መሪነት የተካሄዱት የኣንገዛም ባይነት ኣመጾችና
ጦርነቶች የኦሮሞ ህዝብ ለሃገሩ ሉኣላዊነትና ለህዝቡ ነፃነት ያደረገው ትግል
ኣካል ናቸው። እነዚህ ሁሉ ጀግኖች ኦሮሞ በመሆናቸው ብቻ ነበር በቅኝ ገዢው
ሃይል ዘንድ በደመኛ ጠላትነት የተፈረጁት።

ከደቡብ ህዝቦች ወገንም እንደ ንጉስ ጦና ባሉ ጀግኖች የተመራው የኣንገብርም
ባይነት ትግል ኣይዘነጋም። በሃይል የተወረሩት ሌሎች በርካታ ነፃ ህዝቦችም
ኣቅማቸው በፈቀደው ልክ ወረራውን ለመቀልበስ ተፋለሙ እንጂ ወራሪውን
ሃይል በጸጋ ኣልተቀበሉም። በመጨረሻው ሰኣት በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ተበልጠ
ው ለመውደቅ ቢገደዱም ከዚያም በሁዋላ ቢሆን በሃይል በተጫነባቸው የጭቆና
ቀንበር ስር ኣሜን ብለው ኣልተገዙም። የነፍጠኛው ወራሪ ሃይል እያስገደደ ኣንገ
ታቸው ላይ የሚያስረውን ኣቢሲኒያዊ ማተብ ባለመቀበል ተፋለሙ።

በሃይሌ ስላሴ ዘመንም የህዝቦቹ ኣንገዛም ባይነት ትግል ይበልጥ ተስፋፍቶ ቀጠለ
እንጂ ኣልበረደም። በሃይል ተወርረው ለገባርነት የተዳረጉ ህዝቦች ሁሉ 'ኢትዮ
ጵያ ሃገራችን ናት፣ ሃይሌ ስላሴ ንጉሳችን ነው' ብለው ኣንገታቸውን ቀና ኣድርገ
ው በኢትዮጵያዊነት የኮሩበት ወቅት ኣልታየም። እንዲያውም በኣያሌ ቦታዎች የ
ህዝቦቹ ኣንገዛም ባይነት ኣመጽ ከነፍጠኛው ኣገዛዝ ቁጥጥር ውጭ የወጣበት ሁኔ
ታ

ነበር የተከሰተው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በ1920ዎቹ ውስጥ የተቀሰቀሰው
የራያ ኦሮሞ ኣመጽ ሁሌም በኣንጋፋነቱ ይታወሳል። የሃይሌ ስላሴ መንግስት የራ
ያ ኦሮሞን ኣልገዛም ባይነት ኣመጽ በእግረኛ ጦር መቁዋቁዋም ኣቅቶት የኣየር
ሃይል ድብደባ ለማካሄድ መገደዱን ታሪክ ሁሌም ይዘክራል። ከዚያ ጊዜ በሁዋላ
ም ቢሆን የወሎ ኦሮሞ ኣልገዛም ባይነት ኣመጽ በጀግናው ሃሰን ኣሜ መሪነት
ዳዌ ላይ መፋፋሙ ተጨማሪ ምሳሌ መሆን ይችላል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በባሌ
ለብዙ ኣመታት ሳያቋዋርጥ የተካሄደው የኦሮሞ ህዝብ ኣመጽ የሃይሌ ስላሴ
መንግስትን ኣጣብቂኝ ውስጥ መክታቱ የሚዘነጋ ኣይደለም።

በተቀሩት የኦሮምያ ኣካባቢዎችም በተለያዩ ጊዜያት የተነሱት የኣንገዛም ባይነት
ኣመጾች ተዘርዝረው የሚያልቁ ኣይደሉም። በፊንፊኔና በሌሎች የኦሮምያ ከተሞ
ች ደግሞ በመጫና ቱለማ ማህበር በኣዲስ መልክ የተስፋፋው የብሄርተኝነት ንቅ
ናቄ በኣጭር ጊዜ ውስጥ የነፍጠኛውን ስርኣት በኣንድ እግሩ ያቆመ ሲሆን ይህ
ም በኦሮሞ ህዝብ የትግል ታሪክ ውስጥ ሰፊ መሰረት ጥሎ ያለፈ ነበር። ኦሮሞ
በባእድ ኣገዛዝ ስር ከቶ ተንበርክኮ መቀጠል እንደማይችል የመጫና ቱለማ ማህ
በር ንቅናቄ በማያወላዳ መልኩ ኣስገነዘበ። ኦሮምያ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉ
ተቃውሞዎች ሲቀጣጠሉ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ተመሳሳይ ገፈት ቀማሽ የሆኑ ሌሎ
ች ብሄሮችና ብሄረሰቦችም በኣፋኙ ስርኣት እግር ስር ኣቀርቅረው መገዛትን ኣል
ፈቀዱም።

ለሃይሌ ስላሴ መንግስት ውድቀት ትልቁ ምክንያት የሆነው ዝነኛው የ1960ዎቹ
የተማሪዎች ኣመጽ ከዚያ በፊት ከነበረው የህዝቦች ኣንገዛም ባይነት ብሶት የተ
ወለደ መሆኑ ኣሌ የሚባል ኣይደለም። የኣንድ ብሄር ፈላጭ ቆራጭነት፣ የኣንድ
ቁዋንቁዋና የኣንድ ሃይማኖት የበላይነት እንዲቀር እንዲሁም በጭቁዋኝና በተጨቁ
ዋኞች መካከል ያለው ግንኙነት እንዲያበቃ በመጠየቅ የተማሪዎቹ ኣመጽ የህዝቦ
ችን እሮሮ ኣስተጋባ። ኢትዮጵያ የህዝቦች እስር ቤት ስለመሆኗም የወቅቱ ተማሪ
ዎች ያላንዳች ፍርሃት ጎላ ባለ ድምጽ መመስከራቸው የህዝቦችን የነፃነት ትግል
ወደ ኣዲስ ምእራፍ ኣሸጋገረው። እንደ ዝነኛው ዋለልኝ መኮንን ያሉ በትውልድ
ከኣማራ ብሄር መሆናቸው የሚነገረው ቆራጥና ኣስተዋይ ተማሪዎች የነፍጠኛው
ወራሪ ሃይል በሌሎች ነፃ ህዝቦች ላይ የዘረጋውን የኣንድ ብሄር የበላይነት በጽኑ
በመቃወም ኢትዮጵያ በርግጥ የተለያዩ ህዝቦች እስር ቤት መሆኗን መመስከራቸ
ው ታሪክ የማይረሳው ሃቅ ነው።

ደርግ ተማሪዎች ያቀጣጠሉትን ኣመጽ በጠመንጃ ሃይል ጠልፎ ወደ ስልጣን ከወ
ጣበት በሁዋላ የብሄርተኞቹን እንቅስቃሴ ለመደምሰስ ጥረት ያድርግ እንጂ እስከ
መጨረሻው ሊሳካለት ኣልቻለም። በተማሪዎቹ መሪ መፈክር ተገድዶ የመሬት
ከበርቴነትን ስርኣት ቢያስቀርም በዚህ የጥገና ለውጥ ብቻ በህዝቦች ዘንድ ተቀባ
ይነትን ማግኘት የማይታሰብ ሆነበት። ደርግ ህዝቦችን እያታለለ በስልጣን ለመቀ
ጠል ብዙ ጥሮ ኣልተሳካለትም። የብሄር ብሄረሰቦች ባህላዊ የዳንኪራ ፕሮግራም
ኣቀነባብሮ ለኣለም ህብረተሰብ በማሳየት ብቻ የህዝቦች እኩልነት የተረጋገጠ ለማስ
መሰል ሙከራ ኣድርጎም ከሸፈበት። በ1979 በተለያዩ የውጭ ሃገራት የታየው
የደርግ *'ህዝብ ለህዝብ'* የሙዚቃ ትርኢት ለዚህ የመንግስቱ ሃይለማርያም
ስርኣት የማስመሰያ ጥረት ኣንዱ ምሳሌ ነበር። ስርኣቱ በውድቀቱ ዋዜማ *'ክፍለ
ሃገር'* ይባል የነበረውን የሃገሪቱን የኣስተዳደር መዋቅር በመቀየር *'ኣስተዳደር*

*ኣካባቢ' እና 'ራስ ገዝ ኣካባቢ'* በተሰኙ ስያሜዎች ተካው። በካርታ ላይ የተደ ረገው የአስተዳደራዊ መዋቅር ለውጡ በተግባር ግን ሲተረጎም አልታየም። ስርአ ቱን ኣመንምኖ ሊገድለው ለተቃረበው የፖለቲካ ደዌም ፈውስ ሆኖ ሊያድነው ኣልቻለም። የህዝቦቹ ዋነኛ ጥያቄ የሃገር ሉኣላዊነትና ህዝባዊ ነፃነትን የመጎናጸፍ ጥያቄ በመሆኑ ይህ ወሳኝ ጥያቄ ፍትሃዊ ምላሽ እስካላገኘ ድረስ ደርግ ከቀደ ሙት ስርኣቶች የተለየ ሆኖ ሊታይ ኣልቻለም። በመጨረሻም የመንግስቱ ሃይለማ ርያም ስርኣት ከስልጣን ሊወገድ የቻለው ለህዝቦች ኣንገብጋቢ የፖለቲካ ጥያቄዎ ች ፍትሃዊና ተገቢ ምላሽ ሊሰጥ ባለመፈለጉ ነበር።

ደርግ የተማሪዎችን የብሄርተኝነት እንቅስቃሴ በጠመንጃ ኣፈሙዝ ጠልፎ ለስልጣ ን መወጣጫነት እንደ ተጠቀመው ሁሉ ወያኔ ህወሃትም ለዘመናት ሳያቋዋርጥ ሲካሄድ የነበረውን የህዝቦች የጸረ ጭቆና ትግል እያስታከከ ራሱን የትግሉ መሪ ኣድርጎ በመሰየም የቀደምት ገዢዎችን ቤተመንግስት ወረሰ። ቀደም ሲል በስልጣ ን ከተፈራረቁት ገዢዎች ሁሉ የተለየ መስሎ ለመታየት ሲልም በህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ቁማር ተጫወተ። ቆምኩለት ለሚለው ህዝብ ጥቅም ሲል የራስን እድል በራስ በመወሰን መብት ያመነ መሆኑ ባይካድም ጥያ ቄው ለጭቆና ኣገዛዝ የተዳረጉ የሌሎች ህዝቦችም ጥያቄ መሆኑን ስለሚገነዘብ ራሱን ችሎ በሁለት እግሩ እስከሚቆም ድረስ ለመላው ህዝቦች መብት የሚቆረቆ ር እያስመሰለ ብዙ ደሰኮረ። ደርግ በሁለት እግሩ መሬት ረግጦ መቆሙን ካረጋ ገጠ በሁዋላ በወቅቱ ዋነኛ የስልጣን ተቀናቃኞቹ የነበሩትን እነ መኢሶንና ኢህአ ፓን ተራ በተራ እንዳስወገዳቸው ሁሉ ወያኔም ዋነኛው ባላንጣውን ኦነግን በማዳከ ም ከተቻለውም በመደምሰስ የሃገሪቷን የፖለቲካ ስልጣን በግሉ ለመቆጣጠር የጭ ካኔ እርምጃዎችን ወሰደ። የኦሮሞና የሌሎች ተመሳሳይ ገፈት ቀማሽ ህዝቦችን ጥያቄ በውሉ የመለሰ ለማስመሰልም በህዝቦች ማንነት ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርኣት ዘርግቻለሁ፣ ካሁን ወዲያ ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ከፈለጉም የራሳቸውን እድል በራሳቸው ወስነው የራሳቸው ነፃ መንግስት የመመ ስረት ህገ መንግስታዊ መብት ተጎናጽፈዋል ሲል ለፈፈ። በወረቀት ላይ የተጻ ፈው ህግ ተግባራዊ እንዲሆን የሚጠይቁትን ሃይሎች ግን በደመኛ ጠላትነት ፈር ጆ በጭካኔ ዘመተባቸው። ወያኔ የህዝቦቹ ትግል በሁሉም ኣቅጣጫ ወጥሮ ይዞት መፈናፈኛ እስከሚያሳጣው ድረስም በወረቀት ላይ የፃፈውን ህግ ወደ ተግባር እን ደማይቀይረው እሙን ነው።

ከትላንት እስከ ዛሬ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ በኣጭሩም ቢሆን መቃኘት ያስፈ ልገው ኢትዮጵያ በህዝቦች መልካም ፍላጎት ሳይሆን በወራሪዎች የጠመንጃ ኣፈ ሙዝ ተመስርታ በጠመንጃ ኣፈሙዝ እየተጠበቀች ከዛሬ የደረሰች ፍትህና ነፃነት የራቃት ኣስተዳደር መሆኗን ለማስታወስ ያህል ነው። ኣንዳንድ የትላንቱ ስርኣት ህልመኞች የወያኔ መንግስት ለስልጣኑ እድሜ ማራዘሚያ ብሎ የሚለፍፋቸውን ጥገናዊ ለውጦች ትልቅ ነገር ኣድርገው *'የህዝቦች ኣንድነት እንዲላላ ተደረገ'* በማለት ቡራ ከረዩ ሲሉ መስማት በርግጥ ኣስቂኝ ነው። ወያኔ ለህዝቦች ማንነት የወረቀት ላይ እውቅና ብቻ በመስጠቱ የሚጮሁት እነዚህ ሃይሎች ወያኔንም ጨምሮ የሌሎች ወገኖች መሳቂያና መሳለቂያ እየሆኑ ናቸው። *'በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ትላንት በፍቅርና በደስታ እንደ ኣንድ ብሄር ተዋህዶና ተዋዶ በጋራ የኖረውን ህዝብ እየከፋፈለ ነው'* በማለት ይጮሃሉ። እነዚህ ወገኖ ች በመሬት ላይ ያለውን እውነታ ኣምነው እንዲቀበሉ ማስታወስ የግድ ይሆናል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተዳደሩ የሚገኙ ህዝቦች በራሳች
ው መልካም ፈቃድ ኢትዮጵያ የምትባል የጋራ ሃገር ኣልመሰረቱም። ብሄራዊ
ማንነታቸውን የሁዋሊት በመተው ኢትዮጵያዊ ማንነትን ያስቀደሙበት ወቅትም
ኣልነበረም። የደርግ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' መሪ መፈክርም ይህንን እውነታ ለመ
ካድ ያለመ ቢሆንም መፈክሩ በህልምነት ብቻ የቀረውም ለዚሁ ነው። ሌላው
ቀርቶ ከመቶ ኣመታት በላይ በሃይል የተጫነባቸውን ብሄራዊ የስራ ቋንቋዋ
በወጉ መናገር እንኳዋን የሚችሉት ከህዝቦቹመካከል ምን ያህል ናቸው የሚለው
ራሱን የቻለ ጥያቄ ነው። በምኒሊክ ዘመን በጠመንጃ ኣፈሙዝ እንዲገብሩ ተደር
ገው ኣንደ ኣንድ ሃገር የታወጁት ህዝቦች ናቸው ዛሬም በጠመንጃ ኣፈሙዝ ኣን
ድ ላይ ታጉረው እየተጠበቁ ያሉት። በነዚህ ህዝቦችና በሃይል ባገቷቸው ገዢዎች
መካከል እርቅ የሚባል ነገር ተካህዶ ኣያውቅም። የህዝቦቹ ፍላጎት የተጠየቀበት
ወቅትም ኣልነበረም። በሽግግር መንግስቱ ዘመን ተጀምሮ የነበረው ጥረትም ሩቅ
ሳይሄድ በወያኔ ህወሃት ኣምባገነናዊ እርምጃ እንደተጨናገፈ ኣይዘነጋም። እነዚህ
ህዝቦች ከወያኔ ኣስተዳደር በፊትም ቢሆን በኢትዮጵያዊነት እስር ቤት በሃይል
ታጉረው የቆዩ ናቸው፣ ኣሁን በወያኔው ዘመንም እድላቸው ይሄው ነው። ስለሆነ
ም ኢትዮጵያ ትላንትም ሆነ ዛሬ የተለያዩ ህዝቦች መታጎሪያ እስር ቤት ነች እን
ጂ ህዝቦቹ በራሳቸው ፍላጎት ተፈቃቅደው የመሰረቷት የጋራ ኣገራቸው ኣይደለች
ም። ከዚህ እውነታ መሸሽ የትም ኣያደርስም።

የወያኔ መንግስት ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውን ተግባራ
ዊ እንዲያደርጉ የፈቀደ ይመስል በባዶ ሜዳ የሚጨሁት ወገኖች እነማን እንደሆ
ኑ ለማወቅ ኣያዳግትም። እንዲህ ኣይነቱን ጩሄት በስፋት የሚያሰሙት ያው የኣ
ንድን ብሄር የበላይነት ለመመለስ ዛሬም ከመድከም ያልተቆጠቡት የታሪክ ህልመ
ኞች ናቸው። እነዚህ ጉደኞች እየጠለቀች በምትገኘው የግፍ ዘመን ጀምበራ
ቸው እንጂ እየቀደደ ባለው የፍትህ ዘመን ጎህ ማመን ኣይችሉም። ሙሉ በሙሉ
መሽቶ ድቅድቅ ጨለማ እስከሚውጣቸው ድረስ ተጨባጩን እውነታ ኣይተው
መቀበል ኣቅቶኣቸዋል።

ሌሎቹ የዚህ ጩሄት ተሳታፊዎች ካሉ ምናልባት የኢትዮጵያን ታሪክ በተመለከተ
ያላቸው እውቀት ውሱን የሆነ ተቃዋሚ ተብዬ ወገኖች ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱ
ም በስመ ወያኔ ተቃዋሚነት ራሳቸውን ስላደራጁ ብቻ ኣይናቸውን ጨፍነው የኣ
ሮጌውን ስርኣት ህልመኞች የዳንኪራ ቅኝት እየተከተሉ ከበሮ የሚደልቁ ናቸው።
የህልመኞቹን ቃላት እየኮረጁ ከማስተጋባት ውጪ የራሳቸው የሆነ የፖለቲካ ኣላ
ማም ሆነ ፍልስፍና የላቸውም። እንዲህ ያሉት ወገኖች የኢትዮጵያን የፖለቲካ
ታሪክ በሚገባ በማጥናት የራሳቸውን የማይናወጥ ኣቋዋም እንዲይዙ መምከር ኣስ
ፈላጊ ይሆናል።

በሶስተኛ ኣካልነት የህልመኞችን ጩሄት ኣልፎ ኣልፎ የሚያስተጋቡ ሌሎች
ጥቂት ወገኖችም ኣልጠፉም። ምንም ኣይነት የኣማራነት ደም ሳይኖራቸው የቀድ
ሞው ስርኣት የስነ ልቦና ምርኮኞች በመሆናቸው ብቻ በከንቱ ሲደክሙ ይታያሉ
። ከራሳቸው ጋር ተጣልተው ሌላውን ለመምሰል የሚዳዱም ይመስላሉ።
እነዚህን ከገዛ ጊቢያቸው ኣበባ እየነቀሉ ወስደው ሌላው ሰው ጊቢ ውስጥ ለመት

ከል በከንቱ ለሚለፉ ወገኖች እባካችሁ ንቁና ራሳችሁን ሁኑ ከማለት ባለፈ የምን ለግሳቸው ምክር ኣይኖርም።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ